በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

## በከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ወበት ቢሮ

## የከተሞች ጽዳት አገልግሎት፣ ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት

# የአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሳያ ፕሮፋይል /Indicative Profiles/

ግንቦት 2008 ዓ.ም
አዲስ
አበባ

# ማውጫ


**1. መግቢያ ............ 1**

**2. የአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ............ 2**

2.1. ተቋማዊ አደረጃጀትና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ............ 2

2.2. የደረቅ ቆሻሻ ዓይነቶች ............ 2

2.3. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ ............ 3

2.4. ቆሻሻን የማዛዝና የማስወገድ ሁኔታ ............ 4

2.5. ሃብትን ማስተዳደር /ቆሻሻን ከምንጩመቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፥ መልሶ ኡደት/ ............ 4

2.6. ተደራሽነትና ሁሉን አቀፋዊነት/ INCLUSIVITY/ ............ 4

2.7. የገንዘብ ምንጮችና ማሰብሰቢያ ዘዴዎች ............ 4

2.8. የህግ ማዕቀፎች ተፈፃሚነት ............ 5

2.9. የተለዩ ክፍተቶችና ማነቆዎች ............ 5

2.10. የአሰባሰብ ስርዓትን በተመለከተ ............ 5

2.11. አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ............ 5

2.12. ቆሻሻን መቀነስ፣ መልሶ መጠቀምና መልሶ ኡደትን በተመለከተ ............ 5

2.13. የፅዳት አገልግሎት ተደራሽነትና ሁሉ አቀፋዊነትን በተመለከተ ............ 6

2.14. ፋይናንስን በተመለከተ ............ 6

2.15. የህግ ማዕቀፍ ተፈፃሚነትን በተመለከተ ............ 6

2.16. ተቋማዊ አቅምን በተመለከተ ............ 7

**3. ማጠቃለያ ............ 7**

# 1. መግቢያ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የወጣውን የከተማ አካባቢ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 65/1995 ተከትሎ የአዳማ ከተማ ራሱን የቻለና በልዩ ዞን ደረጃ የተከለለ በመሃል ኢትዮጵያ የምትገኝና ከአዲስ አበባ 99 ኪሎ ሜትር ርቀት የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ አዳማ የሚለው ቃል ከኦሮምኛው ቃል አዳሚ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም የግራር ዛፍ ማለት ነው፡፡ ይህ ስያሜ ቀደም ሲል የነበረ ሲሆን በቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት እአአ ከ1944 ዓም ጀምሮ ናዝሬት በመባል ሲጠራ የነበረና ከ1991 ዓሽም በኋላ በሽግግር መንግስቱ ወቅት የኦሮሚያ ክልል የከተማውን መጠሪያ ወደ ቀድሞው አዳማ እንዲቀየር አድርጓል፡፡ የከተማው የቆዳ ስፋት ከ133 ሺህ ሄክታር በላይ ነው፡፡

ለተሻለ የከተማ አስተዳደር ሲባል የከተማው አስተዳደር ሁለት የአስተዳደር እርከን የተዋቀረ ነው፡፡ አንደኛው የአዳማ ከተማ ማስተዳድር (Adama City State) ሲሆን የሚምራው በከተማው ከንቲባ Mayor ነው፡፡ ሁለተኛው የከተማው ማዘጋጃ ቤት (Adama Municipality) ሲሆን ይህም የሚምራው በከተማው ሥራ አስኪያጅ (City Manager) ነው፡፡ የከተማው ከንቲባ ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤት ሲሆን በተዋረድ የከተማው ማዘጋጃ ቤትና ሌሎች የከተማው ቢሮዎችና ማስሪያ ቤቶች በሙሉ ተጠሪነታቸው ለከተማው ከንቲባ ነው፡፡ በአደማ ከተማ 14 የከተማ እና 4 የገጠር ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን በ2005 ዓ.ም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አጀንሲ ያወጣው መረጃ የከተማው ሕዝብ ብዛት በ2008 ዓ.ም 338,940 ይሆናል ተብሎ ተገምቷል፡፡

እንደ ሌሎች የአገራችን ከተሞች በአዳማ ከተማ የከተማ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጠው በማዘጋጃ ቤቱ በሚገኘው የጽዳት፣ ወበትና አረንጓዴ ልማት የሥራ ሂደት ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም መንግስቱና አሰግድ የተባሉ ግለሰቦች እንዳጠኑት ጥናት መሰረት በአዳማ ከተማ ከመንገድ ላይ በየዓመቱ 3750 ሜትር ኩብ ደረቅ ቆሻሻ የሚመነጭ ሲሆን ከዚህ ወስጥ 2340 ሜትር ኩብ ወይም 63 በመቶ በማዘጋጃ ቤቱ ሰራተኞች ተሰብስቦ በአግባቡ ይወገዳል፡፡ በከተማው የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ መጠን በተመለከተ አብዛኛው አባወራ/እማወራ ወይም 75 በመቶ እና 30 በመቶ ድርጅቶች በሳምንት ከ25 ኪሎ ግራም በታች ቆሻሻ የሚያመነጩ ሲሆን 21 በመቶ አባወራ/እማወራ እና 40 በመቶ ሌሎች በሳምንት 25-50 ኪሎ ግራም እንደሚያመነጩ ተጠቁሟል፡፡




ስዕል1፡- የአዳማ/ናዝሬት ከተማ ከአዲስ አበባ አንፃራዊ መገኛ/ Location/

# 2. የአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት

## 2.1. *ተቋማዊ አደረጃጀትና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት*

በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች የሚከናወኑ ው በከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ስር ያለው የፅዳትና ውበት የሥራ ሂደት ነው፡፡ የከተማው ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ...... የማዘጋጃ ቤቱ ተቀጣሪ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን የመንገድ ላይ ጽዳት የሚከናወነ ወም በነዚህ ሰራተኞች ነው፡፡ በስራ ሂደቱ ያሉ ሰራተኞች ...... በመቶ ከሙያው ጋር ምንም የሚገናኝ ስልጠና የሌላቸው ሲሆን፤ ...... በመቶ የሚሆነ ው የሥራ መደብም ሰው/ባለሙያ ያልተመደበበት ነው፡፡


## 2.2. *የደረቅ ቆሻሻ ዓይነ ቶች*

በአዳማ ከተማ ከሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ ዓይነት 70 በመቶ አርጋኒክ ወይም ሊበሰብስ የሚችል የቆሻሻ ዓይነት ነው፡፡ ከመኖሪያ ቤት ከሚ ነጨው የደረቅ ቆሻሻ ዓይነት የምግብ ተረፈ ምርት እና የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ከፍተኛ ድርሻ ያለቸው ሲሆን ከድርጅቶች የሚመነጨው ቆሻሻ ፕላስቲክና ወረቀት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የከተማው ደረቅ ቆሻሻ ዓይነት (በመቶኛ)

| የቁስ ዓይነት | ከመኖሪያ ቤት | ከድርጅቶች | አማካይ |
|---|---|---|---|
| የምግብ ተረፈ ምርት | 42 | 14 | 28 |
| ቅጠላ ቅጠሎች | 16 | 4 | 10 |
| ወረቀት | 12 | 17 | 14.5 |
| ብረት | 1 | 12 | 6.5 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጨርቅ | 2 | 4 | 3 |
| ፕላስቲክ | 20 | 26 | 23 |
| ማስታወት | 1 | 15 | 8 |
| የተለያዩ | 6 | 8 | 7 |
| ጠቅላላ | 100 | 100 | 100 |




ስዕል2፡ – የአዳማ ከተማ አማካይ የደረቅ ቆሻሻ ዓይነቶች (%)

አብዛኛው የከተማ ነዋሪ የደረቅ ቆሻሻ በማጠራቀም ቤት ለቤት የማሰብሰብ አገልግሎት ለሚሰጡ በጥቃቅንና አነስተኛ ማሕበር ለተደራጁ አባላት የሚያስረክቡ ሲሆን፤ የደረቅ ቆሻሻ የሚከበስቦት በተለያየ ሁኔታ ነው፡፡ 85 በመቶ አባወራ/እማወራ እና 50 በመቶ ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻን በማዳበሪያ ሰብስበው በማቆየት እንዲወገድ ያደርጋሉ፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዓይነት (በመቶኛ)

| **የቁስ ዓይነት** | **መኖሪያ ቤት** | **ድርጅት** |
|---|---|---|
| የተቆፈረ ጉድጓድ | 3 | 10 |
| ከረጢትና ፕላስቲክ | 2 | 20 |
| ማዳበሪያ | 85 | 50 |
| ፕላስቲክ | 7 | 15 |
| ካርቶን | 3 | 5 |
| **ጠቅላላ** | **100** | **100** |

## 2.3. *የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ*

በአዳማ ከተማ ያለው የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ደካማና ከፍተኛ የአቅም ክፍተት ያለበት ነው፡፡ ከሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ ...... በመቶ ብቻ በአግባቡ ተሰብስቦ ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚወገድ ነው፤
የከተማው ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ....... የማዘጋጃ ቤቱ ተቀጣሪ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን የመንገድ ላይ ጽዳት የሚከናወነውም በነዚህ ሰራተኞች ነው፡፡ የከተማው ደረቅ ቆሻሻ በሁለት የማዘጋጃ ቤቱ የገንዳ መጫኛ መኪናዎች እና በአራት የማህበራት ተሽከርካሪዎች በመጓጓዝ ተሰብስቦ ከከተማው 9 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /uncontrolled dumping site/ ይወገዳል፡፡ የጤና እና ደህንነት ማጠበቂያ አገልግሎት ሥርዓት የለም፡፡ በከተማው ዘመናዊ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /ሳኒተሪ ላንድፊል/ የለም፡፡

## 2.4. ቆሻሻን የማያዝና የማስወገድ ሁኔታ

በከተማዋ በቀን ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ማለትም ....... ቶን ....... በመቶ በቻ በማዘጋጃ ቤቱ ሰራተኞችና በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ተሰብስቦ ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚደርስ ሲሆን ....... በመቶ የሚሆነው የከተማው ቆሻሻ የሚወገደው በየሜዳው፣ በየቦዩ እና አንዳንደም በዘልማድ በማቃጠል ነው፡፡

## 2.5. ሃብትን ማስተዳደር /ቆሻሻን ከምንጩመቀነስ፣ መልሶ ማጠቀም፣ መልሶ ኡደት/

እንደ ሌሎች የአገራችን ከተሞች በአዳማ ከተማ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩበመቀነስ፣ በመልሶ ማጠቀምና በመልሶ ኡደት ዘርፍ ያለው እንቅስቃሴ ዝቅተኛ ከሚባሉት ከተሞች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ ቆሻሻን ከምንጩለመቀነስ እንዲቻል የማለየት ስራ በከተማ ደረጃ ብዙ የተሰራ ሥራ የለም፡፡ በከተማ ቆሻሻን መልሶ ለማጠቀም አንዳንድ ቀልዝ/ኮምፖስት የማዘጋጀት ሥራዎች ያሉ ቢሆንም ያን ያህል የተጠናከረ አይደለም፡፡ መልሶ ኡደት በተማከለ በከተማው የሚጠቀስ ሥራ የሌለ ሲሆን፤ ይሉቁንም መደበኛ ባልሆነ መልኩ ከቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ብረታ ብረቶችንና ፕላስቲኮችን በመልቀም ለራሳቸው ጥቅም የሚያወሉ አንዳንድ ግለሰቦች አሉ፡፡

## 2.6. ተደራሽነትና ሁሉን አቀፋዊነት/ Inclusivity/

በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት ተደራሽነት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም አገልግሎቱን የሚያገኙት መኖሪያ ቤቶች ብዙ አይደሉም፡፡ በከተማዋ ጽዳት ጉዳይ የሕብረተሰብ ተሳትፎ እጅግ ወሱን ነወ፤ በመሆኑም አብዛኛው ነዋሪ ቆሻሻን በተገኙ ክፍት ቦታዎች ያስወግዳል፡፡ የሕብረተሰብ ትምህርትና ግንዛቤን ለማሳደግ ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች /ከጤና ጥበቃ፣ ከአካባቢ ጽ/ቤትና ከሌሎች ከሚመለከታቸው/ ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡ ምንም እንኳን ዝቅተኛ የግንዛቤ ለውጥ ያለ ቢሆንም ሕብረተሰቡ በጽዳት ዘመቻ ይሳተፋል፡፡ በዘርፉ የግሉን ዘርፍ ሊያሳትፍ የሚችል የሕግ ማዕቀፍ ያለ ቢሆንም ግልጽ ለሆነ አሰራር ክፍተቶች አሉበት፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ምንም ዓይነት የግል ድርጅት ወይም ተቋም የለም፡፡ የአገልግሎት ፈላጊው ተሰሚነት እና የሕብረተሰብ ተሳትፎም እጅግ በጣም ዝቅተኛና ወሱን ነወ፤ የኅብረሰብ ትምህርና ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ እንዲሁም በተደጋጋሚ ለሚነሱ ቅሬታዎችና ሮሮዎች ተገቢወን እና አፋጣኝ ምላሽና ግብረ-መልስ የማስጠት ስርዓት የለም፡፡

## 2.7. የገንዘብ ምንጮችና ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

እንደ ሌሎች ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች በአዳማ ከተማ ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚመደበው በጀትና የፋይናንስ ምንጭ ከከተማው ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ በከተማው አስተዳደር የሚመደበው በጀት ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለከተማ አረንጓዴ ልማትም ነው፡፡ በአሁኑ ግዜ ከየቤቱ ለሚሰበሰበስ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ከብር 10 እስከ 30 በወር ይከፈላል፡፡ እንደ ሌሎች ከተሞች በማስወገጃ ቦታ ለሚወገድ ደረቅ ቆሻሻም ማዘጋጃ ቤቱ የሚያስከፍለው ክፍያ የለም፡፡ ገቢን ከማሳደግና የዘርፉን የፋይናንስ አቅም ከማሳደግ አንጻር የክፍያ ስርዓቱን በወቃ ላይ ለማድረግ በሂደት ላይ ነው

## 2.8. የህግ ማዕቀፎች ተፈፃሚነት

የዘርፉን ልማት የሚሚከቱ በፌደራል ደረጃ የተዘጋጁ የሕግ ማዕቀፎች ማለትም የአካባቢ ፖሊሲ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ 513/1999፣ ብሔራዊ የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስታንዳርድ፣ ወዘተ ያሉ ቢሆንም በክልልና ከተማ ደረጃ ይህን ያህል የተዘጋጁ የዘርፉን ልማት ሊመሩ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች የሉም፡፡

ለዚህ ደካማት በምክንያትነት የሚወሰደው ማዘጋጃ ቤቱ ከክልልጋር ያለው ትብብርና ቅንጅት ዝቅተኛ መሆን፣ የፋይናንስ እጥረት፣ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር እና የሚጠው የቴክኒክ ድጋፍ አናሳ መሆን የማሰሉት ናቸው፡፡ ስለሆነም ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ካልሆነ በስተቀር በአካባቢ ጽዳትና ጥበቃ የሚደረግ የቁጥጥር ስራ የለም፡፡

## 2.9. የተለዩ ክፍተቶችና ማነቆዎች

### 2.10. የአሰባሰብ ስርዓትን በተመለከተ

- በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ደካማ በመሆኑ የሚሰበሰበው 30 በመቶ ብቻ መሆኑ፣
- 70 በመቶ የሚሆነው ቆሻሻ በየቦታው መወገዱ ወይም መቃጠሉ፣
- የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ቆሻሻ የማሰብሰብ ሥራ በማዘጋጃ ቤቱ የቀን ሰራተኞች በአንድ ሚጓጓዣ ትራክተር ብቻ እየታገዘ የሚከናወን መሆኑ፣
- ማዘጋጃ ቤቱ በርካታ ገንዳዎች ቢኖሩትም ለእነሱ ማንሻ የሚያገለግል ተሽከርካሪ አለመኖር፣
- በዘርፉ ለተሰማሩ ሰራተኞች የጤና ደህንነት ጉዳይ እንዲሁም ደህንነት ማጠቢያ ቁሳቁሶች ትኩረት ያልተሰጠ መሆኑ፣
- የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት በተመለከተ ዝቅተኛ ደረጃ መሆን፣

### 2.11. አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ

- በከተማው ከሚመነጨው ቆሻሻ 30 በመቶ ብቻ ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚወገድ መሆኑ
- በከተማው ያለው የማስወገጃ ቦታ ለዘርፉ የተቀመጠውን ስታንዳርድ የሚያሟላ መሆኑ፣
- በማስወገጃ ቦታ የሚወገደው ቆሻሻ ለቃጠሎ የተጋለጠና ከዚህም የጭስ ብክለት መኖር፣
- በማስወገጃ ቦታው ላይ በአካባው አርሶ አደሮች እንዲነሳላቸው አቤቱታ የቀረበበት መሆን፣

### 2.12. ቆሻሻን መቀነስ፣ መልሶ ማጠቀምና መልሶ ኡደትን በተመለከተ

- በአዳማ ከተማ ያለው ቆሻሻን የማሰብሰብ አገልግሎት በጣም ደከማ መሆኑ፣
- ቆሻሻን ለይቶ የማሰብሰብ ስራ ወሱን መሆን፣
- ከቆሻሻ ቀልዝ/ኮምፖስት እና ብሪኬት የማዘጋጀት ጥረት አለመኖር፣
- ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ የተሰጠ ትኩረት አለመኖር፣
- በመልሶ ማጠቀም ላይ ለማተፍ ወሱን አቅም መኖር፣

## 2.13. *የፅዳት አገልግሎት ተደራሽነትና ሁሉ አቀፋዊነትን በተማከተ*

- በከተማው ከስ ቦታዎች ላይ የሚኙ ዝቅተኛ ገቢ ነዋሪዎች  አግባብነት ያለው የፅዳት አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸው፣
- የሕብረተሰብ ትምህርትና ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ የአቅም ወስንነት መኖር፣
- ሕብረተሰቡ በሚሰጠው አገልግሎትና በተለይም በማስወገጃ ቦታው ከፍተኛ ቅሬታ ያለው መሆኑ፣
- ተጠያቂነትን ያሰፈነና በውጤት ማመላከቻዎች የታገዘ ግልጽ የአሰራር ችግር መኖር፣
- በዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ላይ የሕብረተሰብ ተሳትፎ አለመኖር፣
- በዘርፉ ያለው የደመዎዝ ክፍያ ዝቅተኛ መሆን በአገልገሎቱ ላይ ስጋት የተጋረጠ መሆኑ፣
- በአጠቃላይ በዘርፉ የሚሰጠው አገልግሎት በዝቅትኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆን፣

## 2.14. *ፋይናንስን በተማከተ*

- ወቅታዊ ለዘርፉ ልማት በማዘጋጃ ቤቱ የተመደበው በጀት እጅግ አነስተኛ መሆኑ፣
- እንደ ሌሎች ከተሞች በወሊሶ ከተማ ለዘርፉ የሚመደበው በጀት ከከተማ አረንጓዴነት ልማት ጋር የሚጋራ መሆኑ፣
- ማዘጋጃ ቤቱ ለዘርፉ ልማት የተለያ አካወንት የሌለው በመሆኑ ለዘርፉ የሚመደብለትን በጀት ለመረዳት ችግር መኖር፣ በ2007 ዓ.ም በዘርፉ የወጣ ወጭ የማዘጋጃ ቤቱን 11 በመቶ መሆኑ
- በዘርፉ ለሚሰጠው አገልግሎት የወጪ ማካካሻ ስርዓት አለመኖር፣
- እንደሌሎች የአገራችን ከተሞች በከተማው ቆሻሻ ማስወገጃ ክፍያ አለመኖር፣
- በዘላቂ የፋይናንስ ምንጭ ከተማው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ፣

## 2.15. *የህግ ማዕቀፍ ተፈፃሚነትን በተማከተ*

- የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት አደረጃጀትና ኃላፊነት በተሻለ ደረጃ ለመደራጀት የተቋም፣ የቴክኒክና የፋይናንስ አቅም ወስንነት መኖር፣
- በከተማ ደረጃ የፌደራል ህጎችን፣ ፖሊሲዎችንና ስታንዳርዶችን ለማስፈፀም ከፍተኛ ፋይናንስ  አቅም ወሱንነት መኖር፣
- በክልል ደረጃ ያለው ቅንጅትና ትብብር ደካማ መሆን፣
- የፌደራል ፖሊሲዎችና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማስተማር የሚያስችል ደረጃወን የጠበቀ ሀገራዊ የህዝብ ማስተማሪያ እና ማሰልጠኛ ዘዴዎች አለመኖር፣
- የተበጣጠሰና የተወራረሰ ኃላፊነቶች በባለድረሻ አካልት መኖር፣
- ለዘርፉ አሰራር ብሔራዊ የፋይናንስ ድጋፍ አለመኖሩ፣

- የተደራጀና ሳይንሳዊ የሆነ ሀገራዊ የሚረጃ ቋት አለመኖሩ ወጡታማ እቅድ ለማዘድና ክትትልና ቁጥጥር ለሚድረግ የሚያስችሉ ሚልካም አጋጣሚዎችን በእጅጉ የሚቀንሱ ሚሆናቸው፣

## 2.16. *ተቋማዊ አቅምን በተማለከተ*

- በከተማው ላለው ወቅታዊና ደካማ አገልግሎት ዋናው ምክንያት ከተቋማዊ አደረጃጀት ይልቅ የፋይናንስ ችግር ሚሆኑ፣
- በዘርፉ የኦፕሬሽን ቁሳቁሶችና ጥገና፣ ላንድፊል ዲዛይንና ኦፕሬሽን፣ የማንገድ ፕላን፣ የሚልሶ ኡደት ቴክኒኮች፣ የቁሳቁስ ማስፈረቶችን… ወዘተ ያካተተ ስልጠና አለመኖር፣
- የፋይናንስ እጥረት የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ለማዘርጋት እንቅፋት ሚሆኑ፣
- ለአካባያዊ ፖሊሲና እንቅስቃሴ ትኩረት ማስጠትና ጠንካራ የክትትል ስርዓት አለመኖር፣
- የተሰሩ ሥራዎችንና የወጡ ወጪዎችን ለመመዝገብ የሚያስችል የሚረጃ አያየዝና አስተዳዳር ስርዓት ደካማ ሚሆን፣
- በወሳኝ የሥራ መደብ ላይ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ እንዲሁም ካለው የሥራ መደብ 40 በመቶ ክፍት ሚሆን፣

## 3. ማጠቃለያ

የአዳማ ከተማ ለአዲስ አባባ ከተማ ካላት ቅርበት አንጻር በከፍተኛ ዕድገት ላይ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ የነዋሪዎቿም ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ በመሆኑም ከነዋሪው ሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር የሚጣጣም የማስረተ ልማትና የአገልግሎት ተቋማት በሚፈለገው ማጠን እና ፍጥነት ማሳደግ የወቅቱ የከተማዋ ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ አዳማን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግና የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ማዕከል ለሚድረግ በስፋት ሊሰራባት ከማገባ ማስረተ ልማት አንዱ የከተማ ጽዳት አገልግሎት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ፕሮፋይል ወስጥ የተጠቀሱ የዘርፉ ዋና ዋና ክፍተቶችንና ማነቆዎችን ማስረት በሚድረግ የመፍትሄ እቅጣጫዎችን ማስቀመጥና ወደ ተግባር መግባት ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም የህብረሰተቡን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓትን በተደራጀ አግባብ ማጠናከር፣ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለማሻፈን እንዲቻል ገቢን በተሻለ ደረጃ ማሳደግ፣ በዘርፉ ሊሰሜሩ የሚችሉ ማህበራትን የሚደራጀትና አቅም በማንባት ወደ ስራ ማስገባት፣ እንዲሁም ከተማው የሚስጠዉን የጽዳት አገልግሎት ሽፋን ለማሻሻልና አገልግሎቱን በሁሉም አካባቢ ተደራሽ ለሚድረግ አስፈላጊ የሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ማምቻቸት ይገባል፡፡

**ማስታወሻ፤** ለዚህ ለአዳማ ከተማ ፕሮፋይል ዝግጅት የሚረጃ ምንጭ ከኢንተርኔት የተገኘው Solid Waste Management in Adama, Ethiopia: Aspects and Challenges, by Mengist Hailemariam, Assegid Ajeme; World Academy of Science, Engineering and Technology International Journal of Environmental, Chemical, Ecological, Geological and Geophysical Engineering Vol:8, No:9, 2014 ጽሑፍ ነው